# የአክራሪ እስልምናን እንቅስቃሴ ለመቋቋም በሚደረግ የመፍትሔ ውይይት ለመነሻ የሚያገለግል ረቂቅ ሐሳብ

**1.** ***መግቢያ*** :- የእስልምና ሃይማኖት እንቅስቃሴ በሀገራችን መካሔድ የተጀመረው ከሰባተኛው ምዕት ዓመት ጀምሮ ቢሆንም ከግራኝ ወረራ በቀር በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች ኢትዮጵያውያን መካከል በአጠቃላይ አመለካከት የመቻቻል አኗኗር የታየበት ብዙዎችም እንደ አረአያ አድርገው የሚያነሱት ነው። አሁን በቅርቡ የተፈነጠቀው የአክራሪ እስልምና እንቅስቃሴ ግን በአንጻሩ የሽብርተኛነትን ጠባይ ያቀፈ ሆኖ በታሪክ ሂደት የነበረውን (ጠባብም ቢሆን) የአብሮ መኖርን ህይወት እያደፈረሰው ይገኛል። በውይይት እንደታየው የአሸባሪዎች እንቅስቃሴ ዛሬ የሚያሰጋ ደረጃ በመድረሱ ለመቋቋምና ለመግታት አጸፋውን መመለስ ማስፈለጉ ጉልህ ክሥተት ነው።

በሁለተኛ መንገድ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ የእስልምና አማኞች ቁጥር ሰፊ በመሆኑ የሁለቱ ሃይማኖቶች ተከታዮች ተከባብረውና ተቻችለው የሚኖሩበት መንገድና ዘዴ እየተቀየሰ በየጊዜው እየታደሰ መኖር እንዳለበት ስሌት ውስጥ መግባት አለበት።

በሥስተኛ ደረጃ ለብዙ ዘመን ሰላም መሰል ግንኙነትን ያደፈረሰው ምንድር ነው ቢባል በተቀዳሚ ከሀገር ውጭ የተፈጠሩና የተቋቋሙ አክራሪና አሸባሪ የአረብ ሀገሮችና ድርጅቶች ድጋፍና ተጽዕኖ ሲሆን እንደአጋጣሚ ሆኖ ደግሞ በቤተ ክህነት አሠራር የሚገባውን በጥበብና በቆራጥነት የተመሠረተ የአመራር አቋም አለመዘጋጀቱ ነው።

እንደዚሁ ያለውን ውስብስብ እይታ አንድ ዓይነት መልክ ወይም አቅጣጫ የያዘ መንገድ ወይም ዘዴ እንደማይፈታው የታወቀ ነው። ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ሀሳብ ከሌሎች ድርጅቶችና ተቆርቋሪዎች ጋር በመተባበር ጤናማና ጠንካራ መፍትሔ የሚሆን አሰባሳቢ አካል ለማቋቋም በሚደረግ ውይይት በመነሻነት እንዲያገለግል ታስቦ የቀረበ ረቂቅ ነው።

***<u>የሚቋቋመው አካል (ድርጅት ወይም ማኅበር) ዓላማ</u>***

*የሚቋቋመው ድርጅት መሠረታዊ ዓላማ*

1.1 ምዕመኑን ስለ አክራሪና ሽብርተኛ እስልምና እንቅስቃሴ በተከታታይ መረጃና ትምህርት ለመስጠትና ለማሰጠት፤
1.2 የችግሩን አሳሳቢነትና ወቅታዊነትም በመረዳት በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ መንፈሳዊ ኮሌጆችና ከፍተኛ ትምህርት ቤቶች ከመመረቃቸው በፊት አንድ ወቅታዊ መረጃዎችና እንቅስቃሴዎችን ያካተተ ኮርስ እንዲሰጣቸው እንዲደረግ ለማሳሰብ፤
1.3 አሁን በማገልገል ላይ ላሉት መምህራን ደግሞ አጭር የማሠልጠን ኮርስ እንዲሰጣቸው የኮርሱን ይዘትና ማስተማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት

አስተማሪዎችና አቀነባባሪ ድርጅት እንዲቋቋም ለማገዝ፤ካለም በጎኑ ለመቆም፤

1.4 በውጭው ዓለም በዲያስፖራ ላለው ምዕመንና መምህራን እንዲሁ እንደዚህ ያለ ጉባዔ በማዘጋጀት የመረጃ ውይይት እንዲቀርብ ለማዘጋጀት፤
1.5 የቤተክርስቲያናችንን ጤንነትና ደኅንነት በሚመለከት ጉዳይ ሁሉ የሚሰለፍ የደኅንነት ጠባቂ ግብረ ኃይል ለማቋቋም ወይም የተቋቋመ ድርጅት ካለ ይኽንን ሥራ እንዲከታታል ለማገዝ፤
1.6 በሁለቱ ሃይማኖቶች መካከል ውይይት እንዲካሔድ ለማመቻቸት
1.7 አልፎ አልፎ የሥራውን እንቅስቃሴ በልዩ ልዩ መገናኛ ዘዴዎች ለሕዝብ እንዲደርስ ለማድረግ፤
1.8 እነዚህ ሀሳቦች ሊጨመርባቸው ወይም ሊጠቃለሉ ይቻላል፡፡

## 2. <u>አስተባባሪ አካል ወይም ግብረ ኃይል</u>

ከላይ በተራ ቁጥር 2 የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ፈቃድና ችሎታ ያለው አካል የካህናትና የምዕመናን ጉባዔ መቋቋም ይኖርበታል ወይም የጉባዔው ሥራ አመራር የክትትሉን ኃላፊነት መውሰድ ይኖርበታል፡፡ አንድ ራሱን የቻለ አካል ወይም ግብረ ኃይል ይቋቋም ቢባል የአካሉ ወይም የግብረ ኃይሉ አባላት እንዴት ይመረጡ? ለመነሻ ያህል አባላቱ በመጀመሪያ ከሚከተሉት ልዩ ልዩ ድርጅቶች ቢወከሉ አመራረጡ ግን ውክልና ብቻ ሳይሆን ችሎታንም ያቀፈ ግለሰብ እንዲመረጥ ጥንቃቄ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ለምሳሌ

2.1 ከምዕራብ ሀገሮች የካህናትና የምዕመናን ጉባዔ የሚወከል ወይም የሚወከሉ፤
2.2 ከሰባክያን ማህበር ቡድን የሚወከል፤
2.3 ከወገን ነፍስ አድን ኮሚቴ የሚወከል፤
2.4 ከአብነት ት/ቤቶች ማጠናከሪያ ድርጅት የሚወከል፤
2.5 ከማኅበረ ቅዱሳን የሚወከል፤
2.6 ለቤተ ክርስቲያናቸው ባላቸው ታማኝነታቸውና በችሎታቸው በመታወቅ በግለሰብ ደረጃ የሚመረጡ
2.7 ሌሎች ካሉ